# ነጋሪት

ከሥርጉተ ሥላሴ - ህዳር 2003 ዓ.ም

ተጎስሞብኝ እና ባተትኩ። የውሸት እንዳይመስላችሁ የእውነት ነው። ከዛ ትንሽ ተግ ብዬ አደምጥከት። ጨኸቱ ናላ ያዞራል። አናት ይበጠብጣል። ሸሽት ጀመርኩ። ፈጠንኩ። እርጥኩ። ግን ተከተለኝ። ላምልጠው አልቻልኩም ሊጨብጠኝ ገሰገሰ እኔም ደመ ነፈሴን ተፍጨረጨርኩ። ኃይሌን ሰብሰብ አድርጌ ሸመጠጥኩ።

... ግን የት እንደምጓዝ አላውቀውም። መነሻዬ እራሱ ጠፍቶብኛል። እንኳንስ መድረሻዬ ... ። ብቻ እንደ ወጀቡ አቀጣጫዬን ስቼ እንዳልወጣ ወይም ብን ብዬ እነዳልጠፋ ከራሴ ጋር ተፋጠጥኩ። አሸናፊም ተሸናፊም ለነገሩ የለም ብዬ ተጽናናሁ።

ደግሞ ይህን እያወጣሁ እያወረድኩ አያ አጀሬ ጉርበዬን እንዳያንቀኝ የሙትሙቴን ድፈረትን የሙጥኝ ብዬ ቀጠልኩ። ቀጠልኩ። እንዳልቀልጥ ግን ሰጋሁ። አቅልጥ ቅልጥ እንዳያረገኝ ወይም ከበረድ ጋር እንዳያጋባኝ ሰጋሁ።

... ስጋቴ ስጋትን ሊግተኝ ተፈተታ ተነኝ ።አሻም ብዬ አፈንግጬ አሁንም ሮጥኩ መድረሻዬ የት ሊሆን እንደሚችል ግን እንኳንስ ባላንጣዬ እኔም አራሴ አላውቀውም ብቻ ለማምለጥ ግብግብ። አሁንም ነጋሪቱ ጉራውን እሱ ይቸረችራል። ደረሰኩ መጣሁ አነቅኩሽ ይለኛል። እኔም ፈጣሪዬን ተማምኜ መጪ አልኩ። ግን ወደዬት? .... አይተወቅም። ብቻ የእሱ ሰለባ ከመሆን እሄድኩ መሞትን መረጥኩ መሮጥ መገስገስ በቃ ....

ቃ ... ያለው መንፈሴም ተከተለኝ። ለነገሩ ደርቋል። በቀኝ በግራ ተውጥሮ። ምንስ ፋታ አግኝቶ ይለዝብ፤ ፈርዶበት። እንዲህ ያለ ዕጣ ፈንታ ከኔ ተፈጥሮ ታመስ ተነገረገበ ... ። የደከመው ሲተወኝ አዲሱ ጉለበተኛ በተራው ተነስቶ ያሸኛል፤ እስኪቢቀው ይደልቀኛል፤ ያው የበቀል አምላክ የእጁን ይስጠው እንጅ ሰላሜን ቀምቶ ያባትለኛል ...

ደግሞ ከሱ ጋር ተዳብሎ የሚያምሰኝ አልበቃ ብሎ እኔም የእሱ እድምተኛ ወይንም ማህበርተኛ ቁበኛ እንድሆን ነጋ ጠባ ይወተውተኛል አሻፈረኝ ስለው ደግሞ መላሾ ቢጤ ያዘጋጅ እና በእራፊ ሊታረቀኝ ይሞዳሞዳል። መድሚዳ! የበቀል ሙዳ ... የግለኝነት ብርንዶ አሰናድቶ ይጎስማል ይጎስማል። ሊያጠምደኝ ይከተለኛል። አልሻም ስለው ይገፋኛል። ይገፈትረኛል። አድሞ ያሳድምብኛል .... አቤት ለአንዲት ምስኪን ትቢያ ላለለች ኢሚኒት ፍጥረት እግዚብሄር የእጁን ይስጠው ... ለቀፎው ..

ባዶ እኮ ነው ጭድ ... ምንም የለውም ያው ሰንበር ግን ያለው ይመስለኛል። ቸርቸር የሚያደርግብት። ግን እሰከ መቼ? አይታወቅም ዝም ብሎ ይነዳል። የሚገርመኝ ህሊና አለኝ የሚለውም ከ እሱ ጋር አብሮ መንጎዱ። አይገርም! አለመሆን ትልቅ ነገር። ይህ ቢቀር ደግሞ አልመተባበበር አንድ ነገር። ነገር ግን ተዳብሎ ይሁን ተቀላቅሎ፣ ተዘንቆ ይሁን ተቀላቅሎ፤ ፋታ ነስቶ መማስ አይገርም? ... እሾህ የምድር እንቧይ ...

ይጎስማል ይጎስማል መጣሁ ሄድኩ እያለ ያምሳል፣ ያተራምሳል፣ ይፈጫል፣ ይደልቃል፣ ጉራ ይጭናል፣ ይሽቅጣል ይቅባል ጥላሸት ይቀባል ... ግን የለም እኮ በቦታው ምደረ በዳ ነው ጠፍ፣ የመከነ፤ የፈለሰ ጉድ፤ ግን ዝም ብሎ ይጮኃል ... ይጮኃል ... አንደ ቀን ግን እንክት ስበር ብሎ ይፈልሳል፤ ቆይ ታዩታላችሁ ... የቆዬ ሰው ይይው፤ ይህን አራሞቻ የግለኝነት ባላንባራስ - ማንቆ መንጠቆ ... ጥበቆ!

ወ ይ ጉድ ምንንም፣ ግን እንዲያው ምንም፤ እንዲያው ምንም የሌለው እንዲህ እግር ከወርች አስሮ ለዛውም ደግሞ አባራሪ ሆኖ ቁጭ ... ዘመን የሰጠው አሉ ... ብቻ ይሁን ደህና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ አሉ ጠፋ ሰው ... እና ባዶ ደግሞ ከሰው ተቆጥሮ እንዲህ አና እንዲያ ይገርማል ....